# መልካም አመራር

በዶር ኤረንነ ቀልብሰው

ይኖርበታል አመራር፣ መሆን መልካም ምሳሌ፣
የሕዝብ ፍጹም አገልጋይ፣ እንደ ታማኝ ሎሌ።
    አመለካከቱ የቀና፣ ሕዝቡን የሚሰማ፣
    አቅሙን የሚያውቅ፣ በወገን ፍቅር የተጠማ።
ዳኝነቱ ሚዛናዊ፣ ካንዱ ለሌላ የማያዳላ፣
በሰው ልጅ ዕኩልነት፣ እምነቱ የተመላ።
    የሌላውን ፍላጎት፣ ከራሱ የማይለይ፣
    አገልግሎቱን የሚሰጥ፣ ፊጥኖ ለባለጉዳይ።
ሥልጣን ጊዜያዊ እንደሆነ፣ ጠንቆቅ የሚያውቅ፣
በተንኮል ያልተካነ፣ ተግባሩ ያልሆነ ድብቅ።
    መልካም ለማድረግ፣ ሁሌ የሚጥር፣
    ስህተት ላለመድገም፣ ከታሪክ የሚማር።
ችግርን ከሕዝብ ጋር፣ አብሮ የሚጋፈጥ፣
ወገን በስቃይ ትቶ፣ ለራሱ የማይፈረጥጥ።
    ወቃሽ ህሊና ያለው፣ በጥቅም የማይደለል፣
    በማገልገሉ ደስ የሚሰኝ፣ የሚጠላ የሌላውን በደል።
ልጅ የሚንከባከብ፣ አዛውንት የሚያከብር፣
ለመማር ዝግጁ፣ ከልምድ የሚሻ ምክር።
    የሕዝብን ችግር የሚረዳ፣ የሚያጽናና በመከራ፣
    የወገን አለኝታ፣ የማይናወጥ ተራራ።
ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ የአንድነትን መሠረት፣
ይቅርታን የሚያበልጥ፣ አለመግባባት ባለበት።
    ደሃ ሀብታም ሳይል፣ ሁሉን እኩል አገልጋይ፣
    አድሎ የማይታይበት፣ "ነግ በእኔ ባይ"።
ጥሩ ወላጅ ይመስል፣ ትሁት አስተማሪ፣
የሃይማኖት አባት፣ የነፍሳት አፍቃሪ።
    ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ዜጋ ሁሉ በየሙያው፣
    እንዲሠሩ ማበረታታት፣ የሆነ ሥራው።
ለሕዝብ ጥቅም፣ አርቆ የሚያስብ፣ የሚያቅድ፣
የማይገኝ ዕንቁ ነው፣ ዋጋው በጣም ውድ።
    ወጣት፣ አዛውንት፣ ተራ ዜጋ፣ ባለሥልጣን፣
    ሁሉን የሚመራ፣ ከጨለማ ወደ ብርሃን።
በስህተት የማያሾፍ፣ የሚያርም በትዕግሥት፣
ያልተመላ በትዕቢት፣ ዘወትር የሚከተል እውነት።
    ለበጎ ሥራ ቀስቃሽ፣ ተግባሩ ማስተባበር፣
    ሁሌ ተግቶ የሚሠራ፣ ኑሮ እንዲሻሻል ባገር።
በማስገደድ የማያምን፣ ሰው የማያስቀይም አውራ፣
ለሕዝብ የሚጠነቀቅ፣ በስህተት እንዳይመራ።
    ቅም በቀል የማይሻ፣ ለአመለካከት ልዩነት፣
    ሁሌ ሰላም ፈላጊ፣ በማሰብ ላገር ዕድት።
ወገን እንዲያልፍለት፣ እንዲመለስ ታሪካችን፣
መልካም አመራር፣ ያስፈልጋል ባገራችን።